የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ጥቅምት 23 ቀን 2002 ዓ.ም

# በወያኔ ምርጫ ባልት አለመሳተፍ የዜግነት ግዴታ ነው

በመጪው ግንቦት የወያኔ አገዛዝ በሚያካሂደው ወጤቱ ከወዲሁ የታወቀለት ምርጫ ውስጥ ዜጎች መሳተፍ የለባቸውም:: ለወያኔ አገዛዝ ሽፋኝ ግልድምና ሽርጥ መሆን አይገባቸውም:: የደም ዛር የያዘው ሥርዓት በ1997ቱ ምርጫ ሲሸነፍ ሕዝብን ፈጅቶና የሕዝብን ድምፅ ሰርቆ በጉልበቱ በሥልጣን መቀጠሉን ዜጎች ሁሉ የታዘቡት ምፀት ነውና ዛሬ የሕዝብ መሠረተዊ ጥያቄዎች ጭራሽም ቅንጣትም ምላሽ ሳያገኙ አረመኔው አገዛዝ በአሸናፊነት በሚወጣበት ምርጫ መግባቱ ለሀገርም ለሕዝብም የሚጠቅም እርምጃ አይደለም::

ምርጫ የተባለውን ሂደት በተመለከተ መሠረታዊው ችግር የስነ-ሥርዓትና የስነ ምግባር ሳይሆን ሀገሪቷ በአንድ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ሥር መሆኗና ለነፃ ምርጫ ምንም ዕድል አለመኖሩ ነው:: ካለፈው የዞረ የሕዝብ ሰቆቃ ድምር ደግሞ፣

- የሕዝብ ድምፅ መሰረቁን
- ከ200 ያላነሰ ዜጋ መፈጀቱንና ገዳዮቹ ለፍርድ አለመቅረባቸውን
- ወደ 50 ሺህ የሚጠጉ ዜጎች ተይዘው መታሰራቸውንና ከነዚህም ውስጥ አሁንም ብዙ ሺዎች (ተለቃ ዳግም የታሰረችውን ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳን ጨምሮ) በማጎሪያ ቤት መሆናቸውን
- የምርጫው ህግ አለመቀየሩን
- የምርጫው ኮሚሽን የወያኔ አገዛዝ መሣሪያ እንጂ ነፃ አለመሆኑን
- ወታደሩ ፖሊሱና የፀጥታው ኃይል በቡድኑ ቁጥጥር ሥር መሆናቸውና በየምርጫ ጣቢያዎቹ መራጩን ከማስፈራራት አልፈው ጭፍን የሆነ ግድያና ጭፍጨፋ ማካሄዳቸውን

ያሳያል:: ከ1997 ወዲህ ምንም የተሻሻለ ሁኔታ የለም:: የወያኔ ፈላጭ ቆራጭ ቁጥጥርና አፈና ተባብሷል:: በማስገደድ የድርጅት አባል ሁኑ እየተባለ፣ አባል ተብዬው ቁጥሩ ብዙ ሚሊዮን ሆኗል:: ምርጫ ማጭበርበር መቀጠሉንም ያለፈው የማሟያ ምርጫ ውጤት በግልፅ ዳግም አሳይቶ የባዕዳንንም አፋዊ ወገዛ አድርሶበታል:: መዋቅሩ በእጁ፣ ገንዘቡ በእጁ፣ መገናኛ ብዙሀን በእጁ (በ1997 የነበሩ ነፃ ጋዜጦች ዛሬ በኃይል ጠፍተዋል)--በዚህ ሁኔታ ነፃ ምርጫ እንዴትስ ይጠበቃል?

ኢሕአፓ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት የራሱን የመሰለውን አቅዋም የመውሰድ መብቱን የሚጋፋ ባይሆንም በራሱ መርህና እምነት ደረጃ ግን በወያኔ ምርጫ መሳተፍ ስህተትና ለወያኔ አገዛዝ ብቻ የሚጠቅም ነው ብሎ ስለሚያምን ሕዝብ በመጪው ምርጫ እንዳይሳተፍ ጥሪ ያደርጋል፡፡ በወያኔ ቧልት ከመሳተፍ ይልቅ የወያኔን አረመኔ አገዛዝ ለማስወገድ ለወሳኙ ሕዝባዊ አመፅና ሁለገብ ትግል ዜጎች ሁሉ እንዲዘጋጁና እንዲደራጁ ጥሪ እያደረገ በዚሁ ትግል የተሰማሩና ሊሰማሩ የተነሱት ሁሉ ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እስከታገሉ ድረስ ኢሕአፓ አጋራቸው መሆኑን እንዲያውቁት ያሳስባል፡፡

ለወሳኙ ፀረ ወያኔ ፍልሚያ እንነሳ!

**EPRP**
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

**EPRP**
BP 22
Bois Colombes 92270
France

**E-mail** ESPIC@aol.com **Website:** http://www.EPRP.com